# መምህራን የስካሁኑ ጥረቶቻችሁን እናደንቃለን፤ ለላቀ የትምህርት ጥራት እንድትረባረቡም ጥሪያችንን እናቀርባለን!

(ከብአዴን ማ/ኮ/ጽ/ቤት በአማራ ክልል የተከበረዉን የመምህራን ቀን በማስመልከት የተላለፈ መልዕክት)

## I. መግቢያ

የአማራ ክልል ህዝቦች ጥንታዊ ህዝቦች ናቸው፤ ጥንታዊ ህዝቦች ናቸው በምንልበት ወቅት ግብርና ልማትን በመጀመርና በማስፋፋት፣ በኪነ ህንፃ ጥበብ፣ በባህልና በኃይማኖት፣ የራሳቸውን ፊደላት ቀርፀው ቋንቋቸውን በማሳደግ እና ክብርና ሞገሳቸውን ጠብቀው ጠላትን በማሳፈር የሚታወቁና ከሌሎች ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ጋርም በግብረገብነት የሚኖሩ፣ መልካም ግንኙነት ያላቸው ሰው አክባሪ ህዝቦች ናቸው፡፡

እነዚህ ጥሩ ፀጋዎች የነበሩንና አሁንም ያሉ ሆነው ሳለ እነዚህ ጥረቶቻችን በትምህርትና ትምህርት በሚፈጥረው ዕውቀት የተደገፉ ባለመሆናቸው ለዘመናት ተወስነው ኖረዋል፡፡

ተወስነው መኖር ብቻ ሳይሆን ድህነትና ኋላቀርነት በተገቢው ሁኔታ ሳይሰበሩ በመቅረታቸው ከዚሁ ጋር የመጣ ማይምነት የፈጠረው ኋላቀርነትና ከኋላቀርነት ጋር ተመጋጋቢ የሆነው ድህነት ህብረተሰባችንን ሲያንገላታ እንደኖረ በጣም ግልፅ ነው፡፡ ድህነትና ኋላቀርነት ተንሠራፍተው እንዲቆዩና ዕድሜ እንዲያገኙ ምክንያት ከሆኑት ጉዳዮች አንዱና ዋነኛው የዘመናዊ ትምህርት በሚፈለገው ፍጥነትና ጥራት አለመስፋፋት ነው፡፡ የዘመናዊ ትምህርት በሚፈለገው ጥራት አለመስፋፋት ደግሞ ሳይንሳዊ አስተሳሰብና ቴክኖሎጂ እንዲሁም የሳይንስ አስተሳሰብና ቴክኖሎጂ ተጠቃሚነት ሳይስፋፉ እንደ ሰማይ ርቆን ቆይቷል፡፡ ዘመናዊ ትምህርት ባልተስፋፋበት ሳይንስና ቴክኖሎጂ ሊስፋፉና አገልግሎት ሊሰጡ አይችሉም፤ ሳይንስና ቴክኖሎጂ አገልግሎት ባልሰጡበት ሁኔታ ደግሞ የተሻሻሉ አሠራሮችና ቴክኖሎጂዎች ተግባራዊ ሆነው ህይወትን ሊቀይሩ አይችሉም፡፡ የተሻሻሉ አሠራሮችና ቴክኖሎጂዎች ባልተስፋፉበት ሁኔታ ደግሞ ምርትና ምርታማነት፣ ዕውቀትና ብልሃት በሚፈለገው ደረጃ ሊዳብር አይችልም፡፡ ምርትና ምርታማነት ባልተስፋፋበት ሁኔታ ደግሞ ድህነትንና ኋላቀርነትን በመገርሰስ ልማትና ብልፅግናን ማረጋገጥ አይቻልም፡፡ ያ ማለት ድህነትና ኋላቀርነት፣ ማይምነትና ድንቁርና ዕድሜ እያገኙ ይሄዳሉ ማለት ነው፡፡

ከላይ ከተጠቀሱት ጭብጦች አኳያ ባለፉት 23 ዓመታት በአማራ ክልልም ሆነ በኢትዮጵያ የተለየ ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ የተለየ ሁኔታ ተፈጥሯል በምንልበት ወቅት የኋላ ታሪካችንን በዝርዝር የተገነዘበና ወደፊት በፍጥነት የምንረማመድበትን ሁኔታ ያጤነ የህዳሴ መስመር ቀይሰን ‹‹ትልቅ ነበርን፣ ትልቅ እንሆናለን›› በሚል መንፈስ የልማትና የዴሞክራሲ አቅጣጫ ቀይሰን በጥሩ ጎዳና በመረማመድ ላይ ነን፡፡

ይሄ ትክክለኛ አቅጣጫና ተግባራዊ ጅምር መሠረት ይዞ እንዲቀጥል ዘመናዊ ትምህርት መስፋፋት ነበረበት፡፡ በመሆኑም ባለፉት 23 ዓመታት ዘመናዊ ትምህርትን ከማስፋፋት አኳያ መጠነ ሰፊ ርብርብ ተደርጓል፡፡ በዚህ መጠነ ሰፊ ርብርብ ውስጥ መምህራንና ህዝቡ የላቀ ሚና ነበራቸው፤ ከሁሉም በላይ ደግሞ ለዘመናዊ ትምህርት መስፋፋትና ለሳይንሳዊ አስተሳሰብ መጎልበት መምህራን በገጠር እና በከተማ ሰፊ ርብርብ አድርገዋል፤ እናም መንግሥታችን የመምህራንን ቁልፍ ሚና በመገንዘብ የመምህራን ቀን ለመጀመሪያ ጊዜ ሰኔ 22/2006 ዓ/ም በልዩ ሁኔታ እንዲከበርና መምህራን በተማሪዎቻቸውና በተማሪዎቹ ወላጆች ዘንድ ክብርና ሞገስ እንዲቸራቸው በየደረጃው የሚገኙ አመራሮችም ሆኑ የመንግሥት መዋቅር አካላት የመምህራንን ጥረት እያሰቡ አክብሮታቸውንና አድናቆታቸውን እንዲለግሷቸው፤ የመምህራን ማህበራዊ ሥፍራም ከፍ፣ ከፍ እንዲል ታስቦ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡

ብአዴን/ኢህአዴግ ይህንን ለዕድገትና ብልፅግና ሥራ መሠረት ላለው ዘመናዊ ትምህርት የዚህ ዘመናዊ ትምህርት አባትና እናት የሆኑትን መምህራን ፋይዳ በመገንዘብ መላ ህዝቡ ለመምህራን ተገቢውን ክብር፣ አክብሮትና ፍቅር ይሰጥ ዘንድ ይህን መልዕክት አስተላልፏል፡፡

II. ዘመናዊ ትምህርት ለዕድገትና ብልፅግና ጉዟችን ወሳኝ ቅድመ ሁኔታ ነው

በመግቢያው ላይ በግልፅ እንደተቀመጠው የክልላችን ህዝቦች ጥንታዊና ትልቅ ህዝቦች ሆነው ሳለ፣ የተራቀቁ ፈጠራዎችና ምርጥ ጥበቦች ባለቤት ሆነው ሳለ፣ የያኔው ገናና ታሪካችንና የፈጠራ ተነሳሽነታችን በዘመናዊ ትምህርትና ዘመናዊ ትምህርት በሚፈጥረው የዳበረ አስተሳሰብ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ሳይታገዝና ሳይስፋፋ በመቅረቱ በምትኩ ድህነትና ኋላቀርነት ሰፊ ስፍራ ይዘው ህዝባችንን ሲያንገላቱት ኖረዋል፡፡

ድርጅታችን፣ መንግሥታችንና መላ ህዝባችን በቁጭት ተነስተው ባለፉት 23 ዓመታት የዕድገትና ብልፅግና ቁልፍ መሠረት የሆነውን ትምህርት ለማስፋፋት ሰፊ ርብርብ አድርገዋል፡፡ ዘመናዊ ትምህርትን ለማስፋፋት ተረባርበዋል ስንል የመጀመሪያው የትምህርት ቁልፍ ኃይል የሆነውን መምህር በብዛትና በጥራት የማፍራት ተግባር ነው፡፡ የመምህራንን ቁጥር በብዛትና በስፋት የማፍራት ተግባር የተከናወነው ህዝባችን ሊያገኝ ከሚገባው የዘመናዊ ትምህርት አንፃር ተቃኝቶ ነው፡፡ እናም ከ23 ዓመታት በፊት ቁጥራቸው ከ20 ሺህዎቹ የማይበልጡ መምህራን የነበሩበት ክልል በአሁኑ ወቅት ከ130 ሺህ በላይ አድጓል፡፡ ለዘመናዊ ትምህርት መስፋፋት መምህር አንድ ቁልፍ ግብዓት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የትምህርት ተቋማት መገንባት ነበረባቸው፡፡ በመሆኑም በአንድ ቀበሌ ቢያንስ አንድ፣ ቢበዛ እስከ ሦስት ትምህርት ቤቶች በክልሉ ደግሞ ወደ 8 ሺህ ትምህርት ቤቶችን በመገንባት ወደ 4 ነጥብ 2 ሚሊዮን ህፃናትና ታዳጊዎች ወደ ትምህርት እንዲተጉ እና ዘመናዊ ትምህርት እንዲያጠቃቸው፣ ዕውቀት እንዲገባቸው፣ ሳይንሳዊ አስተሳሰብን እንዲላበሱና ፈጠራና ተነሳሽነት እንዲስፋፋ ፈርጀ ብዙ ጥረቶች እየተካሄዱ ናቸው፡፡

ዘመናዊ ትምህርትን ከማስፋፋት አኳያ መምህራን ቁልፍ ኃይሎች መሆናቸውና ትምህርት ቤቶችና ተማሪዎች ተጣምረው መገናኘት ያለባቸው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የትምህርት ውጤታማነትን ከማረጋገጥ አኳያ በትምህርት ቤቶች ውስጥ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች እና ጠቃሚ የመማር ማስተማር ግብዓቶች ተሟልተው መቅረብ ነበረባቸው፡፡ እነዚህንም ለማሟላት መንግሥትና ህዝብ የተጣመረ ጥረት አካሂደዋል፡፡ በዚህ ንቅናቄ ውስጥ ቅንብሩ የሠመረ እንዲሆን መምህራን ከራሳቸው ድርሻም ባሻገር የህብረተሰቡን ተግባር ጭምር አሟልተው በመፈፀም ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል፡፡ የዘመናዊ ትምህርት ውጤታማነት የሚለካው ሁሉንም ዜጎች ተሳታፊ ከማድረግም በላይ ጥራቱ የተረጋገጠ ትምህርት ማዳረስ ሲቻል ነው፡፡ ጥራቱ የተጠበቀ ትምህርት ለማዳረስ ደግሞ ፈርጀ ብዙ ጥረቶችን ይጠይቃል፡፡ ዋና ዋናዎቹን ለመጥቀስ የመምህር ተማሪ ጥምርታ፣ የክፍል ተማሪ ጥምርታ፣ የመፃህፍት ተማሪ ጥምርታ፣ በሴቶችና ወንዶች ተማሪዎች ጥምረታ የመሳሰሉት ወሳኝ ድርሻ ያላቸው ቢሆኑም ጥራትና ብቃት ያለውን መምህር ድርሻ የሚተኩ ግን አይደሉም፡፡ በሌላ አነጋገር በትምህርት ጥራት ቁልፉ

መምህር ነው፡፡ በጥቅሉ ባለፉት 23 ዓመታት በትምህርት ተሳትፎ፣ በፍትሃዊ ሥርጭትና በፆታ መካከል ያለውን የትምህርት ተደራሽነት ልዩነት በማጥበብና በማቀራረብ የትምህርት ጥራትን በማስፋፋትና በማረጋገጥ፣ ሳይንሳዊ አስተሳሰብ እንዲጎለብት፣ የትምህርት ፍቅርና ተነሳሽነት እንዲታይ መምህራን በገጠር እና በከተማ ፈርጀ ብዙ ጥረት አካሂደዋል፡፡ የመምህራኑን ጥረት የተገነዘበው ህዝብ፣ የመምህራኑን መልዕክት እየተቀበለ ተግባራዊ በማድረግ፣ የልጆቹንና የራሱን አስተሳሰብ ለማሳደግ፣ ከሂደቱም ተጠቃሚ ለመሆን ጥረት አድርጓል፡፡

የህዝብ ተነሳሽነት የመጣው መምህራን ለተማሪዎችና ለወላጆች ባሳዩት ክብርና የለውጥ አስተሳሰብ ግንባታ ነው፡፡ ስለሆነም መምህራን በአማራ ክልል ዘመናዊ ትምህርት እንዲስፋፋና ለገጠሩ አካባቢ እንዲደርስ በአስቸጋሪ ሁኔታም ሳይቀር ላደረጉት ፈርጀ ብዙ ጥረት ላቅ ያለ ክብርና ሞገስ ሊቸራቸው ይገባል፡፡ መሪ ድርጅታችን ብአዴን/ኢህአዴግ በትምህርት ተጠቃሚ በሆነው ህዝብ፣ በተለይ ደግሞ በህፃናትና በታዳጊዎች ስም ከፍ ያለ ክብርና ምስጋና ሊያቀርብላቸው ይወዳል፡፡ ድርጅታችን ብአዴን የመምህራኑ፣ ያስመዘገቡትን በታሪክ የሚወሳ ውጤት በዝርዝር አስቀምጦ ምስጋና ያስቀመጠበት ምክንያት ዘመናዊ ትምህርት የዕድገትና የብልፅግና ሁነኛ መሠረትና ወሳኝ ቅድመ ሁኔታ መሆኑን በማጤን ነው፡፡ ትምህርት ባለፉት ዓመታት በክልላችን ለተመዘገበው ፈጣንና ህዝቡ በየደረጃው ተጠቃሚ መሆን ለጀመረበት ልማት ወሳኝ ግብዓት ሆኖ ስላገለገለ ነው፡፡ ትምህርት መልካም አስተዳደርን ለማስፈንና ዴሞክራሲን እያሳደግን ለመሄድ ወሳኝ ስፍራ ያለው በመሆኑ ነው፡፡ እናም መምህራኑ የፈፀሙትና ያከናወኑት ታሪካዊና ስኬታማ ተግባር በዘመናዊ ትምህርት በራሱ ታጥሮ የሚቀር ሳይሆን በልማትና በዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ሂደት አድርጎ ምልዓተ ህዝቡን ተጠቃሚ ያደረገ ስኬታማና ትውልድ የሚኮራበት ተግባር ነው፡፡ ለዚህ ነው ለመምህራን ከፍ ያለ ክብርና ምስጋና የምንሰጠው፡፡

## III. ዘመናዊ ትምህርት እና ሳይንሳዊ አስተሳሰብ አሁንም የላቀ ርብርብ ይጠይቃል

ክልላችን ብሎም ሃገራችን አሁን ከደረሱበት የዕድገት ደረጃ ተነስተው ወደ ሥልጣኔ ማማ ለመሸጋገር ዘመናዊ ትምህርት አሁን ካለበት የመስፋፋት ደረጃ በላይ መስፋፋት አለበት፡፡ የትምህርት ፍትሃዊነት በዕድሜ፣ በፆታ፣ በአካባቢ ሳይለይ

በእኩልነት መዳረስ አለበት፡፡ የትምህርት መሠረተ ልማት በስፋትና በጥራት ወደ ሁሉም ዜጎቻችን መዳረስ አለበት፤ የትምህርት ግብዓቶች ሳይንሳዊ አመለካከትና ግንዛቤ እንዲሁም ክህሎትን በሚያስጨብጡ አኳኋን በስፋትና በጥልቀት መዳረስ አለባቸው፡፡ የትምህርት ጥራት ከልማታችን ጋር እና ከዴሞክራሲ ጉዟችን ጋር ተገናዝቦ በማያቋርጥ የዕድገት ሂደት ውስጥ መገስገስ አለበት፡፡ በጥቅሉ የትምህርት ተሳትፎና ጥራት ከክልላችን ዕድገት ጋር በተገናዘበ አኳኋን እያደገና እየሠፋ መሄድ አለበት፡፡

እነዚህን ሁሉ ተግባራት ለማከናወን ዋናው የዘመናዊ ትምህርት ባለቤቱና ተጠቃሚው ምልዓተ ህዝቡ ነው፡፡ ምልዓተ ህዝቡ የዕድገትና የብልፅግና ምሰሶ የሆነውን ትምህርት በባለቤትነት እንዲጨብጠው፣ በባለቤትነት እንዲጨብጠው ብቻ ሳይሆን እየተንከባከበ እንዲጠብቀው፣ የአስተሳሰብ ግንባታ፣ የደረጀ የህዝብ እንቅስቃሴን ማቀጣጠል ይጠይቃል፡፡ ተማሪዎች ከህፃን እስከ ታዳጊ ለዘመናዊ ትምህርት፣ ለሳይንሳዊ አስተሳሰብ ተጋላጭ እንዲሆኑ፣ የውድድር መንፈስ እንዲያጎለብቱ፣ በኃላፊነት ስሜትና በትጋት እንዲሠሩ በቂ የግንባታ ሥራ ማካሄድ አለብን፡፡ ይህ ሁሉ ተግባር የሚከናወነው በእስካሁኑ ጉዟችን በአስቸጋሪ ሁኔታ ጭምር ተረማምደው ዘመናዊ ትምህርት እንዲስፋፋ ሲታገሉ የቆዩ መምህራን በእስካሁኑ ጥረታቸው ተበረታትተው ለላቀ የተማሪዎች ዕውቀት ማስጨበጥ፣ ለላቀ ፈጠራና ተነሳሽነት፣ ለላቀ ሳይንስና ቴክኖሎጂ መስፋፋት፣ በጥቅሉ ለክልልና ለሃገር ግንባታ የራሳቸውን ገንቢና በሌላ የማይተካ ሚና ሲጫወቱ ነው፡፡ ይህ የሚሆነው ደግሞ ሁሉ ነገር እንዳሰቡት ተሟልቶላቸው ሳይሆን አስቸጋሪ ሁኔታዎችን ጭምር አልፎ ዜጎችን በዕውቀትና በክህሎት የመገንባት ሥራ በአዲስ የአገር ፍቅር ስሜት እና መንፈስ ሊተገበር ሲችል ነው፡፡ ስለሆነም መምህራኑ ዛሬም እንደ ትናንቱ የላቀ የአስተሳሰብ ከፍታን ማረጋገጥ ይጠበቅባቸዋል፡፡ የላቀ የአስተሳሰብ ከፍታ ሲባል ዘመናዊ ዕውቀትን ወደ ህብረተሰቡ የማስገባት፣ በዚህ የመርካት እና ህዝብን በመጥቀም አድርጎ ለላቀ የህዝብ አገልጋይነት የሚማልል አስተሳሰብን ማጎልበት ማለት ነው፡፡ የአስተሳሰብ ከፍታ ስንል አንደኛው የመምህርነት ሙያን የማፍቀርና የማክበር አመለካከት፣ ህዝብን የማክበርና የማፍቀር አመለካከት እነዚህ … በአመለካከት ከፍታ የሚታዩ ናቸው፡፡

ሌላው መታየት ያለበት የአስተሳሰብ ከፍታ የህዝብ አገልጋይነት መንፈስን የሚያጎድሉ ጎጂና ኋላቀር አስተሳሰቦችን የመታገልና የማስወገድ፣ ከዚሁ ጋር ተሳስሮ የታታሪነትና የሥራ ወዳድነት አመለካከት ማጎልበትን ይጠይቃል፡፡ ከአመለካከት ከፍታ ቀጥሎ በ2ኛ ደረጃ የሚታየው መምህራኑ ክህሎታቸውን በማያቋርጥ ሁኔታ ለማሳደግ መትጋት ልዩ ባህሪያቸው ሊሆን ይገባል፡፡ በሳይንስና ቴክኖሎጂ የተገነባ ትውልድ ለመቅረፅ የሚጠይቀው ልዩ ክህሎት አለ፤ ይሄ ክህሎት ደግሞ መምህራኑ ለሙያቸው፣ በሙያቸው ያላቸውን ክህሎት በየጊዜው እያሳደጉ በልጠው የመገኘትና የተማሪዎቻቸው አርአያና ፋና ወጊ የመሆን ሁኔታ በትኩረት መታየት አለበት፡፡ ሦስተኛው በትኩረት መታየት ያለበት የአደረጃጀት ጉዳይ ነው፤ ጥሩ አመለካከት ቢያዝም፣ ክህሎቱ የተሟላ መምህር ቢኖርም፣ ዜጎቻችንን ለመቅረፅና ሳይንስና ቴክኖሎጂን ለመገንባት የተደራጀ ንቅናቄ ይጠይቃል፡፡ የመምህራንና የተማሪዎች አደረጃጀት የመማር ማስተማሩን በሚያቃናና በሚያጎለብት የሳይንስና ቴክኖሎጂ ምርምርን በሚያፋጥን መልኩ የተደራጀ ንቅናቄ ማካሄድን ይጠይቃል፡፡ ታዳጊ አመለካከት፣ ለማስተማር የሚሆን ክህሎትና አደረጃጀት መያዝ ወሳኝ ቅድመ ሁኔታዎች ቢሆኑም በጠንካራ አሠራር ካልተደገፉ ትውልድን መቅረፅ ቀላል አይሆንም፡፡ አሠራር በምንልበት ወቅት በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ የተቀመጠና ለትምህርት ጥራት መጎልበት የሚበጁ የአፈፃፀም አቅጣጫዎችንና ዝርዝር ተግባራትን አሟልተው መተግበር ማለት ነው፡፡ ይህም አራተኛው የትኩረት መስክ ነው፡፡ እዚህም ላይ መምህራን እስካሁን ያካሄዱትን ፋና ወጊ ንቅናቄ አጠናክረው ማስቀጠል ይገባቸዋል፡፡

ክልላችንና ሃገራችን በማደግ ላይ ያሉ በመሆናቸው የትምህርት ግብዓቶች ውድና በጥንቃቄ ልንጠቀምባቸው የሚገቡ ሀብቶቻችን ናቸው፡፡ ስለሆነም የአደገ አመለካከት፣ ለማስተማር የሚሆን ክህሎት፣ የተደራጀ ንቅናቄ፣ ለውጤት የሚያበቃ አሠራር ብቻ ሳይሆን በትምህርት ቤት ውስጥ የሚገኙ የመርጃ መሣሪያዎችን ጨምሮ ጠቅላላ ግብዓቶችን በውጤታማነትና በአደገ አግባብ ጥቅም ላይ ማዋል ይጠይቃል፡፡ በአጠቃላይ የጀመርነው የልማት እንቅስቃሴ አድጎ ወደ በለፀጉት አገሮች ተርታ ለመሠለፍ ትምህርት ወሳኝ ቁልፍ መሣሪያ ነው፡፡ የዚህ ቁልፍ መሣሪያ ቁልፍ ባለቤት ደግሞ መምህሩ ነው፡፡ መምህራን ባካሄዱት ጥረት ህዝባችንን ተጠቃሚ እያደረጉ ነዉ፡፡ በተለይ አዲሱን ትውልድ የሚገነባ ተግባር

በማከናወን ላይ ናቸዉ፡፡ ለዚህም ምስጋናና ክብር እንደሚገባቸው ብአዴን በጽኑ ያምናል፡፡ በቀጣይም ከላይ የተጠቀሱትን የአቅም ግንባታ መስኮች አሟልተው በመተግበር እንዲረባረቡ በዚህ አጋጣሚ ብአዴን/ኢህአዴግ ጥሪዉን ያስተላልፋል፡፡